Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ስለ ግል ሞባይል መሳሪያዎች መመሪያ የቤተሰብ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቤተሰቦች ስለ ትምህርት አመት 2026–2027 ማወቅ ያለባቸው ነገሮች**

## MCPS ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የግል ስልኮችን/መሳሪያዎችን በትምሕርት ቀናት ቀኑን ሙሉ እንዳይጠቀሙ የሚከለክለው ለምንድነው?

### ጥ፡- በዚህ የትምህርት አመት ይሄ የሚደረገው ለምንድነው?

ሜሪላንድ አዲሱን የስቴት ህግ "Joanne C. Benson Maryland Phone-Free School Act (HB 525)" ማጽደቁ ይታወቃል፤ ይህም እያንዳንዱ የትምህርት ቤቶች ዲስትሪክት በትምህርት ቀን የተማሪዎችን ስልኮች እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን አጠቃቀም የሚገድብ ፖሊሲ መኖር እንዳለበት ይደነግጋል። የስቴት ህጉ በትምህርት አመት 2027–2028 ተግባራዊ ይደረጋል፣ ነገር ግን MCPS አሁን በትምህርት አመት 2026–2027 ሽግግር ማድረግ እየጀመረ ነው፣ ስለዚህ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና ቤተሰቦች የስቴት ህጉ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ሙሉውን አመት እንዲላመዱ ታቅዶ የሚተገበር ነው።

### ጥ፡ MCPS ይህን የሚያደርገው ለምንድን ነው?

ግቡ የተማሪዎችን ጤና፣ ደህንነት፣ እና ሠላማዊ ሁኔታ ለመደገፍ፣ በክፍል ውስጥ ማድረግ ያለባቸውን የመማር ትኩረታቸውን የሚከፋፍሉ ነገሮችን መቀነስ እና ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ለመርዳት ነው።

### ጥ፡ "የግል የእጅ ስልክ/ተንቀሳቃሽ መሣሪያ" (PMD) ምንድን ነው?

ልጆች/ተማሪዎች ከቤታቸው ይዘው የሚመጡት ማንኛውም ከኢንተርኔት ጋር የሚገናኝ/የተገናኘ በድምጽ፣ በቪዲዮ፣ ወይም በጽሑፍ የሚላላኩበት/የሚቀበሉበት ተንቀሳቃሽ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ነው። ይህም ስልኮችን፣ ታብሌቶችን፣ e-readers፣ የግል ላፕቶፖችን፣ ስማርት ሰዓቶችን፣ ስማርት መነጽሮችን፣ እና ማይክሮፎን፣ ካሜራ፣ ድምጽ ማጉያ፣ ወይም የጆሮ ማዳመጫ/earbuds (including AirPods) የመሳሰሉትን መሣሪያዎች በሙሉ ያካትታል። ከትምህርት ቤት የተሰጡ/የሚሰጡ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን አያካትትም።

### ጥ፡- "የአካዳሚክ ቀን" ምንድን ነው?

የትምህርት ቀን ማለት ከመጀመሪያው ደወል እስከ መልቀቂያ ደወል ድረስ ያለውን የትምህርት ቀን በሙሉ ይሸፍናል። ይህም ክፍል ውስጥ ትምህርት የሚማሩበትን ጊዜ፣ የምሳ ሠዓትን፣ የእረፍት ጊዜን፣ እና ኮሪደር ላይ የሚሆኑበትን ጊዜ፣ ወይም መጻዳጃ ቤት በሚጠቀሙበት ጊዜ ሁሉ ያሉትን ጊዜዎች ያካትታል።

## በትምህርት ቀን ውስጥ ያሉት/የሚተገበሩት ህጎች ምን አይነት ናቸው?

### ጥ፡ ልጄ ስልክ ይዞ(ዛ) ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ይችላል/ትችላለች?

አዎን። ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የግል የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ሊኖራቸው ይችላል፣ ነገር ግን በትምህርት ቀን ከመጀመሪያው ደወል ጀምሮ የትምህርት ቀን እስከሚጠናቀቅ ድረስ ለጠቅላላው የትምህርት ቀን የግል ኤሌክቶኒክስ መሣሪያዎቻቸውን ሊጠቀሙ አይችሉም።

### ጥ፡ ልጄ የኤሌክቶኒክስ መሳሪያውን ከትምህርት ቤት በፊት ወይም በኋላ መጠቀም ይችላል?

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

አዎን። ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎቻቸውን የትምህርት ቀን በይፋ ከመጀመሩ በፊት እና በይፋ ከተጠናቀቀ በኋላ የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት የአሠራር ሂደት በመከተል መጠቀም ይችላሉ። ተማሪዎች የዲስትሪክቱን ኃላፊነት የተሞላበት የአጠቃቀም መመሪያ እና ደንብ IGT-RA (MCPS ኔትወርኮችን እና ቴክኖሎጂን ኃላፊነት በተላበት አኳኋን የመጠቀም ህጎችን) መከተል አለባቸው።

## ልዩ ሁኔታስ ሊኖር ይችላል?

አዎ፣ በጥቂት የተወሰኑ ሁኔታዎች ምክንያት በትምህርት ቀን ውስጥ የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ደንቡ ይፈቅዳል፦

- የማንነት ማረጋገጫ፡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የኮሌጅ ቦርድ ወይም IB የመሳሰሉ ድረ-ገጾች ላይ ለመመዝገብ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያቸውን ለአጭር ጊዜ መጠቀም ይችላሉ፣ ይህም በመምህር ፈቃድ እና ቁጥጥር መሆን አለበት።
- የትምህርት ቤት መጓጓዣ፦ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) አውቶቡስ ወይም በቻርተር አውቶቡስ ላይ የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጠቀም ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ የሚፈቀደው የአውቶቡሱን ደህንነት የማያደናቅፍ ከሆነ ብቻ ነው።
- IEP፣ 504 ወይም በሕክምና ሁኔታዎች ምክንያት ከሆነ፡- IEP፣ 504 ፕላን ወይም ሌላ የተረጋገጠ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የጤና ሁኔታቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት ወይም የተፈቀደላቸውን የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አጠቃቀም ለመደገፍ መጠቀም ይችላሉ።
- በአደጋ/በአስቸኳይ ጊዜ ወይም እንክብካቤን የመጠበቅ ፍላጎት ሲኖር፦ ርእሰ መምህራን ለእውነተኛ ድንገተኛ አደጋዎች ወይም ለእንክብካቤ አሰጣጥ አስፈላጊ ሲሆን እያንዳንዱን ጉዳይ በማጤን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ እንዲጠቀሙ መፍቀድ ይችላሉ።
- የቋንቋ ትርጉም፡- ከትምህርት ቤት የሚሰጥ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በማይገኝበት ወይም በቂ በማይሆንበት ጊዜ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎችን ፍላጎት ለመደገፍ ይፈቀድላቸዋል።

### ጥ፡ ልጄ IEP ወይም 504 ፕላን የለውም/የላትም፣ ነገር ግን የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ የመጠቀም ፈቃድ ማግኘት ይቻላል?

አዎን። ርእሰ መምህር ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር፣ መደበኛ IEP ወይም 504 ፕላን ባይኖርም እንኳ የመሳሪያውን አጠቃቀም በማመቻቸት ሊፈቅድ ይችላል። አንዴ ከተፈቀደ በኋላ፣ የተመቻቸው ሁኔታ በተማሪ ፋይል ላይ እንዲቀመጥ ትምህርት ቤቱ ይህንን በሲነርጂ ይመዘግባል።

### ጥያቄ፡- እንደ ድንገተኛ አደጋ የሚቆጠር መሆኑን የሚወስነው ማነው?

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር። ድንገተኛ አደጋ የአንድን ሰው ጤና፣ ደህንነት፣ ወይም ሥላማዊ ሁኔታን በድንገት አደጋ ላይ የሚጥል እና ፈጣን ግንኙነትን የሚጠይቅ ያልተጠበቀ ክስተት ነው። ለምሳሌ፦ ከባድ ሕመም፣ ጉዳት ሲደርስ፣ ከቤተሰብ ጋር፣ ከወላጅ፣ ከአሳዳጊ፣ ወይም ከድንገተኛ አደጋ ምላሽ ሰጪ ጋር መገናኘትን የሚያስፈልግ ክስተት ሲፈጠር ነው።

### ጥ፡ ልጄ በመደበኛ የትምህርት ፈተና ወቅት ስልኩ(ኳ)ን መጠቀም ይችላል/ትችላለች?

የዚህ መልስ በአጠቃላይ አይፈቀድም ነው፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ መደበኛ የትምሕርት ፈተና በሚሰጥበት ወቅት ለፈተናው ደህንነት ሲባል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አጠቃቀምን ይከለክላል። ማንኛውም ልዩ ሁኔታ ከዲስትሪክቱ የግምገማ ቢሮ ፈቃድ የሚፈልግ ሲሆን MCPS የፈተና ደንቦችን መከተል አለበት።

## ኢንተርኔት፣ ደህንነት፣ እና ቁጥጥር

### ጥ፡ ልጄ የትምህርት ቤቱን Wi-Fi ከራሱ(ሷ) የሞባይል ዳታ ጋር ቢጠቀም/ብትጠቀም ምን ለውጥ ያመጣል?

MCPS ጎጂ የሆኑ ይዘቶችን ለማገድ በራሱ አውታረ መረብ ላይ የኢንተርኔት ይዘቶችን ያጣራል። የግል ሴሉላር ግንኙነት ተመሳሳይ ማጣሪያ የለውም። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በይነመረብ/ኔትወርክ ይልቅ በራሳቸው የውሂብ ዕቅድ ኢንተርኔት ጋር ቢገናኙም እንኳ ይህንን ደንብ መከተል ይጠበቅባቸዋል።

### ጥ፡ MCPS ከትምህርት ቤት ኔትወርክ ጋር የተገናኙ መሳሪያዎችን ይቆጣጠራል?

አዎ። MCPS በኔትወርኩ ላይ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ አጠቃቀምን የመከታተል እና የመፈተሽ መብቱ የተጠበቀ ነው።

## ደንቡ ካልተከበረ ምን ይደረጋል?

### ጥ፡ ልጄ መጠቀም በማይፈቀድበት ጊዜ የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ቢጠቀምስ/ብትጠቀም ምን ይሆናል?

ትምህርት ቤቶች MCPS የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ ውስጥ ያለውን የዲሲፕሊን እርምጃ በመጠቀም ምላሽ ይሰጣሉ -- ከማሳሰቢያ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ወይም የባህርይ ማረም ውይይት በመሳሰሉ ዝቅተኛ ገደብ ባላቸው እርምጃዎች ጀምሮ ተገቢውን የዲስፕሊን እርምጃ ይወስዳሉ። ይሄውም ስልኩን እስከመወረስ እና ተማሪ እስኪወስደው ድረስ በትምህርት ቤት የማቆየት እርምጃ ድረስ ሊሆን ይችላል። ተደጋጋሚ የጥሰት ድርጊቶች ተማሪዎች ሞባይል ስልኮቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲያመጡ እስከመከልከል ሊደርስ ይችላል። ሰራተኞች የልጆችን ዕድሜ፣ የእድገት ደረጃ፣ እና ማንኛውንም ተዛማጅ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ያስገባሉ።

**MCPS የተማሪዎች የስነምግባር ደንብ (ሙሉ ሰነድ ጋር የሚገናኝ ሊንክ)**

<table>
<tr><th colspan="8">የተማሪ ስነምግባር እና የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃገብነት ደረጃዎት</th></tr>
<tr><th>አስተዳደር</th><th>ደረጃ 1<br>መማሪያ ክፍል ውስጥ እና በአስተማሪ የሚወሰዱ ምእርምጃዎች</th><th>ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚተገበርና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች</th><th>3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር ውሳኔ እና/ወይም ከት/ቤት የማስወገድ እርምጃ (በትምህርት ቤት ውስጥ የሚወድ የባህርይ ማስተካከል እርምጃ ጣልቃ ገብነት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት)</th><th>ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚወሰድ እርምጃ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል እርምጃ (1-3 ቀናት)</th><th>ደረጃ 5<br>በአስተዳደር ውሳኔ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ (4-10 ቀናት)</th><th>ደረጃ 6<br>በአስተዳደር ውሳኔ ከትምህርት ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ፣ ከት/ቤት የተራዘመ እገዳ (11-44 ቀናት) ወይም ማባረር (45 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት)</th><th>መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።</th></tr>
<tr><td colspan="8">ባህርይ እንዲሻሻል የሚደረግ የዲስፕሊን እርምጃ፣ ጉዳትን የመካስ እና ግንኙነትን መልሶ የመገንባት እርምጃ፣ "የቅጣት እርምጃን ማቅለል" እና "ቅጣትን የማጠንከር" እርምጃ በገጽ 8 ላይ ያሉ መመዘኛዎች ተገቢውን የዲስፕሊን ጣልቃ ገብነት ደረጃ ከመወሰኑ በፊት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።</td></tr>
<tr><td rowspan="5">ተገቢ ያልሆነ የግል ኤሌክትሮኒክስ መገልገያ አጠቃቀም (802)[4]<br>MCPS እነዚህን “የግል ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች” ወይም “PMDs” ይላቸዋል።<br>MCPS ደንቦችን ይመልከቱ፡<br>- COG-RA የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች፣ IGT-RA፣ ለኮምፒውተር ሲስተም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ፣ እና አውታረ መረብ አጠቃቀምን በሚመለከት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች፡-<br>ደህንነት፣ ILA-RA፣ ስለ ደህንነት እና ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች የተደረጉ ግምገማዎች</td><td colspan="2">የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) እና PMDs ደንቦችን በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያን መጠቀም[4,5]</td><td></td><td></td><td></td><td></td><td rowspan="5">ከ MCPS ንብረት የራቀ ሥፍራ ላይ የተፈጸመ የተማሪ ስነምግባር ጉድለት ከት/ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ሲኖረው፣ በአካልም ሆነ ቨርቹዋል የትምህርት አካባቢ ቢሆንም፣ ባህሪው በትምህርት ቤት እያሉ ሌሎች ተማሪዎችን የመጉዳት አደጋ ሲፈጥር፣ ወይም ምግባሩ በትምህርት አካባቢ ላይ የማደናቀፍ ድርጊት የሚያስከትል ከሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።<br>የተማሪ የውሂብ ግላዊነት ጥሰቶች፡- ተማሪዎች ማንኛውንም የግል መለያ መረጃዎችን (PII)፣ ሚስጥራዊ የዲስትሪክት መረጃዎችን፣ ወይም የጓደኞች ወይም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) ሰራተኞችን የግል መረጃ ሠነዶችን (የትምሕርት ውጤት ወረቀቶችን፣ የእኩዮች የሥራ ውጤት ረቂቆችን ወይም የግል መልዕክቶችን ጭምር) ያልተፈቀደ የአርተፊሻል ፈጠራ AI መድረኮች ላይ መለጠፍ፣ ማሠራጨት ወይም ማቅረብ የተከለከለ ነው።<br>የተሳሳተ መረጃ ወይም የተዛባ መረጃ (ማለትም፡- የውሸት መረጃዎች) ማሰራጨት እና በድብቅ PMDs መጠቀም ለተማሪዎች ደህንነት ከፍተኛ አደጋ አለው።</td></tr>
<tr><td></td><td colspan="2">ተማሪ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ MCPS ደንብ በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያ መጠቀም ወይም</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td colspan="2"></td><td colspan="3">6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="2"></td><td colspan="3">የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ PMD መረጃን ማስተላለፍ፣ ግጭቶችን ሪኮርድ ለማድረግ፣ ወይም ከግጭት በኋላ የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ጸያፍ ወይም ስም አጥፊነት ነው፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም MCPS ስራዎችን የሚያስተጓጉል፣ የትምህርት ሂደት ታማኝነትን የሚያጎድፍ፣ ወይም MCPS የኮምፒውተር ሲስተሞችን፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን (የትምሕርት ውጤት ወይም ሌሎች የተማሪ መረጃዎችን ጭምር) ደህንነትን የሚጥስ ድርጊት ማለት ነው።</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="3"></td><td colspan="3">MCPS ኔትወርክን ወይም ስራዎችን በሚያደናቅፍ መልኩ PMD መጠቀም፣ ሪኮርዶችን ለመቀየር ወይም የኤሌክትሮኒክስ ንብረትን ለማጥፋት PMD መጠቀምን ጨምሮ፣ ወይም MCPS በይነመረብን ለማወክ ከውጭ ፕሮክሲ ወይም ቨርቹዋል የመረጃ መሰርሰር ጋር በማጣመር የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (MCPS) መሳሪያን መጠቀም፣ ጉዳት የሚያስከትል አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (ማለትም፡- ውሸቶችን) መጠቀም፣</td></tr>
</table>

**ጥ፡ መምህር ወይም ርእሰ መምህር የልጄን ስልክ ሊወስዱ ይችላሉ?**

አዎ። የትምህርት ቤት ሰራተኞች MCPS ደንቦችን በሚጻረር መልኩ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች እንዲወረስ ማድረግ ይችላሉ።

## የልጄን ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በሚመለከት ተጠያቂው ማነው?

**ጥ፡ የልጄ ስልክ በትምህርት ቤት ቢጠፋ፣ ቢሰረቅ ወይም ቢበላሽ MCPS ተጠያቂ ነው?**

MCPS ተጠያቂ አይደለም። MCPS ለግል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ መጥፋት፣ ስርቆት፣ ብልሽት፣ ወይም ያለፈቃድ መጠቀምን በተመለከተ ኃላፊነት አይወስድም። ቤተሰቦች ልጃቸው ወደ ትምህርት ቤት የግል ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ይዞ እንደሚመጣ/ይዛ እንደምትመጣ ሲወስኑ ይህንን ማመዛዘን አለባቸው።

## ልጄን እንዴት መደገፍ እችላለሁ?

**ጥ፡ በትምህርት ቀን ልጄን በግል ስልኩ(ኳ) ማግኘት እችላለሁን?**

ወላጆች/አሳዳጊዎች በትምህርት ቀን ተማሪዎቻቸውን በቀጥታ በግል ስልካቸው ማነጋገር እንደሌለባቸው ይመከራሉ። ለአስቸኳይ እና አስቸኳይ ያልሆኑ መልእክቶችን በሚመለከት፣ የትምህርት ቤቱን ዋና ቢሮ ማነጋገር ይችላሉ። የትምህርት ቤት ሰራተኞች አስፈላጊ መረጃዎችን ለተማሪዎች በወቅቱ ማድረሳቸውን ያረጋግጣሉ።

**ጥ፡- ትምህርት ቤቱ በትምህርት ቀን ውስጥ የሞባይል ስልክ አጠቃቀም ገደቦችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲያደርግ እንዴት መደገፍ እችላለሁ?**

ቤተሰቦች ስለ MCPS የሞባይል ስልክ አጠቃቀም ፖሊሲ ከተማሪዎቻቸው ጋር እንዲነጋገሩ እና ተማሪዎቻቸውን በሚከተሉት መንገዶች እንዲደግፏቸው እናበረታታለን፡-

- የሞባይል ስልኮችን በተመለከተ ያሉት ደንቦች በትምሕርት ላይ ማድረግ ያለባቸውን ትኩረታቸውን የሚከፋፍሉ ነገሮችን በመቀነስ የመማር እና የማህበራዊ ስሜታዊ ደህንነታቸውን ለመደገፍ የታለሙ መሆናቸውን መወያየትና ማስረዳት፣
- በቤተሰብ ድንገተኛ ሁኔታ/አደጋ ሲያጋጥም (ተማሪን በቀጥታ ከማነጋገር ይልቅ) የትምህርት ቤቱን ቢሮ ማነጋገር።
- አስቸኳይ ያልሆኑ ጉዳዮችን ከትምህርት ቀን በፊት ወይም በኋላ ብቻ ማነጋገር።
- ከተማሪዎች ለሚመጡ አስቸኳይ ያልሆኑ ጽሑፎች ምላሽ ለመስጠት የትምህርት ቀኑ እስኪጠናቀቅ ድረስ መጠበቅ።

**ተጨማሪ ጥያቄዎች አሉዎት?**

ስለ ደንቡ ጥያቄዎች ካሉዎት የትምህርት ቤትዎን ርዕሰመምህር ወይም ዋና ቢሮ ያነጋግሩ ወይም MCPS የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል/Division of School Leadership and Improvement (240) 740-3110 ደውለው ያነጋግሩ።